Institute of Development & Education for Africa, Inc.

**1199 Whitney Ave Suite 523 Hamden, Ct 06517 Tel: 203-789-1990 or 203-747-2763**

November 18, 2014

# Annotated Bibliography of New and Noteworthy Books on Ethiopia

**Ghelawdewos Araia, PhD**

This annotated bibliography on the new and recent publications on Ethiopia is intended to present a brief summary, assessment, evaluation of, and reflection on the books. Some of the books are written in English and others in Amharic, and the bibliography, hence, is in both languages in order to retain the authenticity and originality of the contents of the books as presented by the authors to the reader.

Note: Since all authors are Ethiopians or of Ethiopian origin, in this annotation, although we employ the Chicago Manual Style, we will not use the 'last name, first name' method. Instead, we will preserve the Ethiopian traditional name calling of 'first, last name' style.

**Gedion Wolde Amanuel. <u>'Game Changers' of Identity Politics in Ethiopia.</u> Addis Ababa, 2012**

This book is dedicated to Walelign Mekonnen and Martha Mebrahtu, two prominent leaders of the Ethiopian Student Movement (ESM) and who sacrificed themselves at the Home Front led by the University Students Union of Addis Ababa (USUAA). The bulk of the contents of the book are on the national question or question of nationalities in Ethiopia as propounded and promoted by the ESM. Some articles compiled by the editor also deal with the Eritrean question and subsequent ethnic federalism in Ethiopia.

What makes the book interesting is its presentation of contrasting views and perspectives, as well as some revelations with respect to the complex Ethiopian politics of the 1970s, 1980s and beyond, including some mystery regarding subterfuges, and infiltrations that some organizations suffered from. This book is also significant because it contains seven appendices in Amharic, all but one, authored by Walelign Mekonnen.

**Seyoum Haregot. <u>The Bureaucratic Empire: Serving Emperor Haile Selassie.</u>** Trenton, NJ: The Red Sea Press, 2013

*The Bureaucratic Empire* has five parts and thirty-three chapters, and the contents range from governance to public sector management, to the creeping coup d'etat of the military junta. In between these topics, important themes such as Ethiopia's adverse relations with Somalia, Haile Selassie's visit to China, the arrest of the Aklilu Cabinet, and the rise of the military regime that ended monarchic rule in Ethiopia are thoroughly examined from the author's distinct vantage point, his hindsight, and his performance as professional diplomat at the service of the Emperor.

The book furthermore provides important information in regards to the inner circle of Emperor Haile Selassie's Government and the machinations and convoluted political practice as experienced and witnessed by the author himself.

For review of this book, google the title or open the following link: www.africanidea.org/The%20Bureaucratic_empire_Ghelawdewos_Araia.html

**Bulcha Demeksa. *My Life*: My Vision of the Oromo and Other Peoples of Ethiopia**. Trenton, NJ: The Red Sea Press, 2013

Bulcha Demeksa's book, in many ways, is similar to Seyoum Haregot's book, because both authors were high-ranking government officials in Haile Selassie's Government, and both were insiders in that regime, so to speak. However, while Bulcha is focused on his life, his education, and his financial expertise when he served under Minister Yilma Deressa, Seyoum is more into the politics of Haile Selassie's Government, his involvement in diplomacy, and in his close contact with the Emperor.

The contents of *My Life* essentially reflect the rich and diverse resume of the author. However, while some topics in the many chapters are easy to understand, others that deal with the author's involvement in politics very much reflect controversies and the hard struggles Bulcha waged under his party, the Oromo Federalist Democratic Movement (OFDM) and his association with the Awash International Bank.

For review of the Book, open the following link: www.africanidea.org/My-life.html

**Zewde Gabre-Sellassie. Yohannes IV of Ethiopia: A Political Biography.** Trenton, NJ: The Red Sea Press, 2014

This edition of the book is revised and updated by the author and posthumously published by the Red Sea Press. The Thirteen chapters of the book cover Yohannes' period in the context of power struggle within Ethiopia, the Ethiopian-Egyptian conflict, the reunifications of the Ethiopian regions, the encroachment of the Italians, and the Battle of Metema of 1889 that sealed the fate of Emperor Yohannes and changed the political landscape of the region forever. The chapters are also reinforced by nine appendices that carry important documents, including letters and correspondences exchanged between the contending forces within Ethiopia and outside Ethiopia.

In a nutshell, as Edward Ullendorff, states in his preface to the first edition of the of the Book (1975), "The work embodied in this book represents the fruit of long study and profound knowledge of the events and personalities of the time on the part of the author."

For review of the Book, www.africanidea.org/Yohannes_IV_political_Biography.html

**Ayalew Yimam (Mukhtar). The Ethiopian Student Movement and the National Question.** Maryland, USA: Signature Book Printing, 2013

This book is a compilation of three decades of struggle of the Ethiopian Student Movement in general, and as its title suggests, the question of nationalities, in particular. It is selected and introduced by Ayalew Yimam and Ghelawdewos Araia has contributed

the Foreword. Extracts from the Foreword satisfactorily explicate the contents of the book as follows: *The Ethiopian Student Movement and the National Question: Basic Documents*, complied by Ayalew Yimam, is a result of decades of painstaking collection of data and carefully assembled documents of the Ethiopian Student Movement (ESM) in order to render authenticity to the events that have unfolded during the course of the student upheaval. The distinct advantage of compiling old documents in the form of a book does not only furnish the political agenda, activities, and encounters of the ESM but it also makes it easier for the reader to explore and examine the commitment of the Ethiopian students to the larger Ethiopian society while at the same time serving as a readily available textbook for reference desks in libraries.

**Ghelawdewos Araia. Ethiopia: Democracy, Devolution of Power, and The Developmental State.** Hamden, Ct: Institute of Development and Education for Africa (IDEA), 2013

As its title suggests, this book has three parts that contain seventeen chapters which, in turn, discuss analytic and historical framework; what Ethiopia can learn from American democracy; what Ethiopia can learn from European democracies; what Ethiopia can learn from some African countries; political culture in the Ethiopian context and the mindset of Ethiopians; the contribution of education to Ethiopia's democratic transformation; and institutionalizing democracy in Ethiopia – the last topic of Part I of the Book, includes the following subtitles: what Ethiopia can learn from its own historical experience; preconditions for a democratic Ethiopia; and obstacles to democratization in Ethiopia.

Part II examines a comparative perspective on devolution of power under the Derg regime, and under the EPRDF. However, the chapters in this Part also discuss the evolution and making of modern Ethiopia, with particular focus on the reigning period of the last Emperor in Ethiopian history.

Part III, Chapter 13, is focused on the developmental state and the chapters discuss the political economy of Ethiopia's development agenda in the context of theoretical considerations and vis-à-vis other developmental states such as Japan, the high performing Asian economies collectively known as the Tigers, China, Brazil, India, and Botswana. Chapters 14, 15, and 16 are respectively on agricultural, industrial, and educational developments in Ethiopia; and the final chapter (17) entitled 'Reconciling Democracy, Devolution of Power, and The Developmental State (DS), entertains sub-topics such as 'reinforcing democracy and the DS in the context of democracy and governance; 'the role of the DS in nurturing the domestic economy and attract global investment'; and 'the EPRDF and the future of Ethiopia'.

For review of the Book, please view www.africanidea.org/Tariku_Debretsion.html

**Asayehgn Desta. From Economic Stagnation and Dependency to Democratic Developmental State**. Trenton, NJ: The Red Sea Press, 2014

This book explores the political economy of Ethiopia during the 1930s and 1940s and delves into the human capital and economic changes under Emperor Haile Selassie, and critically examines the 'myth of military socialism' of the Derg. The above themes are discussed in chapters 1 through 4. In chapters 5 through 14, the author explicates important issues surrounding the command economy, ethnic federalism, micro credit for

poverty alleviation, the Japanese Kaiser economic management style, China's south-south cooperation and investments in Africa, economic growth and inflation, the Malaysian development model, and the continuing saga of globalization and comparing Ethiopia's development strategies to that of Malaysia.

From one of the blurbs on the book, Henry M. Levin has the following to say: "This book demonstrates the complexity of economic growth and development and the intertwined relationship between economics and politics. It represents an important interpretation for the historical dynamics of Ethiopia that are also lessons from other countries."

**Addis Alem Balema. Democracy and Economic Development in Ethiopia.** Trenton, NJ: The Red Sea Press, 2014

This work is a PhD dissertation turned a scholarly book and the author discusses important topics and themes such as theory of democracy and economic development; history; transition and political actors; constitutional issues and political reform; devolution of power; the Eritrean question, independence, and its aftermath; economic development under the EPRDF Government; and democracy and economic development in Ethiopia. The above titles are discussed in chapters 1 to 9. Chapter 10 entitled 'Concluding Remarks', is the last chapter of the book and the author discusses the evolution of modern Ethiopia and clarifies his viewpoint (and by default, his position) on the themes of the chapters mentioned above

From one of the blurbs on the book, this is what Andreas Eshete had to say: "Addis Alem Balema addresses the question of how the Federal Democratic Republic of Ethiopia has embarked on the joint pursuit of promoting democratic rule and advancing development, especially the daunting challenge of defeating dire destitution. Whether or not democracy and development are rival or mutually supportive ideals is a widely contested issue in theory and in practice alike. Addis Alem Balema shows how Ethiopia's peculiar circumstances compelled a simultaneous commitment to the quest for political and economic emancipation."

**Solomon Ejigu Gebreselassie. The Ethiopian Peoples Revolutionary Party: Between A Rock and A Hard Place, 1975-2008.** Trenton, NJ: The Red Sea Press, 2014

Solomon Gebresleassie's book is the latest of the many books written in English on the Ethiopian Peoples Revolutionary Party (EPRP) that have mushroomed in recent years as reflections on past experiences, and that have been circulating for public consumption. This book begins with the end game in the context of an urban setting, and according to the author, "it was the beginning of the slide to face more challenging times, and the time that signaled the push to leave the stage for other, anti-Ethiopian opposition actors." This is the opening statement of Chapter One, and under this chapter, themes such as the Youth League, the forced confessions, the Fourth EPRP CC Plenum, internal turmoil, the urban defense wing, relations with the Tigray Peoples Liberation Front (TPLF) and the Eritrean fronts, EPRP in the eyes of foreign writers are thoroughly examined and discussed.

While Chapter Two is essentially about the Ethiopian Peoples Revolutionary Army (EPRA) retreat from Tigray to Eritrea, Chapter Three is a synthesis of the sociological dimension of the struggles waged by the EPRP in relation to women's oppression, the

religious divide, and educating the peasant masses against false beliefs and bad practices. Chapter Four discusses the Second Party Congress and the Ethiopian Democratic Union (EDU) distraction, and Chapter Five is about the 'TPLF confrontation: Round 3'. Chapter Six is about EPRA defection, a narrative that well depicts the consequences of series of conflicts. While Chapter Seven discusses EPRP's relations with China and Sudan, Chapter Eight questions the democratic nature of EPRP. Chapter Nine revisits the women issue touched upon by Chapter Three and elaborates the role of women in the early stages of the EPRP and during the 1974 Revolution. Chapter Ten, the last chapter, is dedicated to EPRP in exile and other opposition groupings that have attempted to form a united front.

**Note: the books published by the Red Sea Press can be obtained by directly calling the publisher at 1-609-695-3200 or 1-609-638-5784**

## ኮንጂት ብርሃን ምርኮኛ 7ተኛ እትም 2006 ዓ.ም.

የቆንጂት ብርሃን ምርኮኛ የተሰኘውን መጽሐፍ ልበ ወለድ ሆኖ እውነተኛ ታሪክን የሚያንጸባርቅ ነው። ታሪኩም ስለ ኢሕአፓ ሕዝባዊ መንግሥትና ነጻነት በኢትዮጵያ ለማንገስ ላደረገው ትግልና ለተከፈለው መስዋእትነት በድራማ-መሳይ ስነጽሑፍ የቀረባ ነው። በዚሁ መጽሐፍ በቅድመ ግንባር ትግሉን ያጧጧፉት በርካታ ተዋንያን ተጠቅሰዋል። ከነዚህም መሃል ደግሞ አንተነህ፣ በላይነህ፣ ቃለአብ፣ ዳንኤል፣ ወ/ሮ ስርጉት፣ ቅዱስ፣ ዘርአይ፣ ጋዲሳ፣ ፈቃደ፣ አስቻለው፣ ታረቀኝ ወዘተ ይገኙበታል። ከሁሉም በላይ ማእከላዊ ቦታ የያዘችው ግን ፍሬሒይወት ናት። እንድያውም መጽሐፉ ስለ ፍሬሒይወት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፣ ምርኮኛዋም እሷ ናት።

ደራሲዋ ለምን መጽሓፉን "ምርኮኛ" እንዳለችው በገጽ 26 ገልጸዋለች፦ "ፍርዬን የሁለት ጦርነቶች ምርኮኛ ሆና አገኘሁዋት እናም ለጽሑፉ ርእስ እንዲሆን ወሰንኩ። ፍርዬ ጀግና ነች፣ በአንደኛው ጦርነት ቁስለኛ ሆና ቆየች፣ በሁለተኛው ጦርነት ግን ሕይዋቷን ነጠቃት።" ይህ አገላለጽ መጽሐፉ ሊገባደድ ሲል በገጽ 469 ይደገምና ሕይወት በገዛ አንደበቷ እንዲህ ትላለች፦ "እንግዲህ ምን ቀረኝ? ሁሉም ነገር አበቃ። የሁለት ጦርነት ተሳታፊ ሆንኩ፣ በሁለቱም ተማረክሁ። ከፖለቲካው ጦርነት ነጻ ወጣሁ፣ የተዘጋጀሁበትና አልሜ የተነሳሁበት ጉዞ በመሆኑ እርምጃየ ሁሉ ወኔ የተሞላበት ነበር…ከሁለተኛም ምርኮም አላመለጥኩም…ወትሮውንም እኮ የለየቱንና ያወቁትን ጠላት መከላከል ቀላል ነው። በጉያ ከሸሸጉት ጠላት ማምለጥ ግን ጠንከር ያለ ውሳኔን ይጠይቃል? ኤች.አይ.ቪ. እንደዛ ነው፣ በማንነት የተሸሸገ ጠላት፣ እናም የራሴን ማንነት ብቻ እያሰብኩ ችላ በማለቴ ከምርኮው ማምለጥ አልቻልኩም።"

መጽሐፉ ስድስት ክፍሎች አሉት፣ የያንዳንዱ ክፍል ርእስ ደግሞ ይዘቱ ምን እንደሆነ ለአንባቢ መላምት ይሰጣል። ደራሲዋ የስነ ጽሁፍ ተስጦ ስላለት ደግሞ ሁሉንም ነገር፡ ማለትም በትግሉ ዙርያ የተካሄዱትን ፖለቲካዊ፡ ሕበረተሰባዊ፡ ግላዊ ነክ ተግባራትን ስዕላዊ በሆነና በተካነ መልኩ በማቀናበር ለአንባብያን አቅርባቸዋለች። የመጽሓፉ ክፍላተ-አካላት የሚከተሉትን ያካተቱ ናቸው፦ ክፍል 1፡ ልጅነትና ዘመቻ፣ ክፍል 2፡ ትግልና ፍቅር፣ ክፍል 3፡ ስደትና እስራት፣ ክፍል 4፡ ሕይወት እንደገና፣ ክፍል 5፡ የትዳር ሕይወት፣ ክፍል 6፡ የመጨረሻው ቀን ሲመጣ።

አስማማው ኃይሉ   <u>ኢሕአሠ (የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት)</u>

ቅጽ ሁለት 2006 ዓ.ም.

ይህ መጽሓፍ ከዚህ ቀደም ደራሲው ከጻፈው የቅጽ አንድ (ኢሕአሠ 1964-1970) ተቀጥያ ሆኖ የሠራዊቱ ታሪክ ከ1970 ዓ.ም. እስከ 1972 ዓ.ም. ያካተተ ነው። መጽሐፉ አስራ ዘጠኝ ምዕራፋትና ሁለት አባሪዎች የያዘ ሲሆን ከሞላ ጎደል የኢሕአሠ ተሞክሮዎች፣ ውጣ ውረዶችም ጭምር፣ በዝርዝር አቅርቧል። ምዕራፍ አንድ፡ ሀለትና ሦስት ኢሕአሠ መጀመርያ እንቅስቃሴ ያደረገበትን የጸለምት ወረዳን አስመልክቶ ያትትና ስለ ሠራዊቱ ከሕዝቡ ጋር መቀላቀል እንዲሁም የአካባቢውን ባህል አስመልክቶ በጥልቀት ያቀርባል።

ምዕራፍ አራት፡ አምስትና ስድስት ስለ ሠራዊቱ በሪጂን መከፋፈል፣ የአዲስ ዘመንና የማይጸምሪ ኦፐረሽኖች፣ እንዲሁም የሠራዊቱና የካድሬው መዋቅር ግንኙነትን አስመልክቶ ሲያቀርቡ፣ ምእራፍ ሰባት ደግሞ በኢሕአፓ የውጭ ግንኙኖቶች ላይ ያተኮረ ነው። ምዕራፍ ዘጠኝ የሪጂን አንድና ሪጂን ሦስት ፓርቲ ኮሚቴዎች ለበላይ አካል ያቀረቡትን ሪፖርት ይዘግብና የበለሳው የካድሬ መዋቅር ቅሬታና አመጽ በሚመለከት የቀረበውን ሪፖርት ያጠናቅራል።

ምዕራፍ አሥር ስለ 'የትግሉ የፈጠራቸው ስሕተቶች' ነቀፌታ-አዘል ትንተና ሆኖ፣ በተለይ ግን ስለ አርባያ ጦርነት መክሸፍ ምክንያት፣ ስለ ተከሰሱ የኃይል መሪዎች፣ በሠራዊቱ በነበሩት አንጃዎች ላይ ስለተወሰደው እርምጃ፣ ከሠራዊቱ ስለተሰናበቱት ግለሰቦች፣ ስለ የዓሲምባው የእርማት እንቅስቃሴ፣ የአባት ጡረተኞች በእብናትና አርባያ ከተሞች መመደብ ወዘተ ያትታል። ምዕራፍ አስራ አንድና አስራ ሁለት ስለ አራተኛው የኢሕአፓ ፕሌኔምና እንድምታው ሲተነትኑ፣ ምዕራፍ አስራ ሦስት ደግሞ ስለ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አገር ወዳድ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኢሕአወደድ) በአርማጭሆ መቋቋምና አንዳንድ የኢሕአፓ አባላትም በድርጅቱ ገብተው እንደነበር ያወሳል።

ምዕራፍ አስራ አራት 'ፍላጎትና ተቃርኖ' በሚል ርእስ ደራሲውና "ሁለት የሠራዊት አባላት ከሪጂኑ ፓርቲ ኮሚቲ የስምሪት ትእዛዝ" እንደተሰጣቸው ያትትና ለሁለት የሚጋጩ ወይም የማይጣጣሙ ሁኔታዎች እንደተጋለጡ፣ ማለትም ደርግ ካደረገው ወረራና ከተከፈለው መስዋእትነት ጋር በማገናዘብ ሂሳዊ ዘገባውን ያቀርባል። ምዕራፍ አስራ አምስት ስለ የሪጂን ሁለት አመራርና የፓርቲው ልኡክ ሆኖ ስለ የሸንፋው ሰሚናርም ይተነትናል።

የምዕራፍ አስራ ስድስት ርእስ፣ "የተነጠቀ ትግል"፣ ከወዲሁ ይዘቱን ለመገመት ባያስቸግርም ዋና ትኩረቱ ግን በልዩ ልዩ ጓዶች ትዝታዎች ላይ ነው። ከተጠቀሱት አንዳንድ የኢሕአሠ ጀግኖች እነ ገብረኪዳን (ገብሬ)፣ ወልዴ፣ ፍቅሬ፣ ግደይ (ጨጓር ዳንጋ) ወዘተ ይገኙበታል። ምዕራፍ አስራ ሰባት ስለ የአባላት የፖለቲካ ንቃት ደረጃ ነው። ምዕራፍ አስራ ስምንት 'የመጨረሻው መጀመርያ' በሚል ርእስ "የሁሉም ሪጂኖች የቅራኔዎች አያያዝ የተለያዩ እንደነበሩ ሁሉ አጨራረሳቸውም እንዲሁ ለየቅል ነበር" ብሎ ይጀምርና "የፓርቲው ልኡካን...የሪጂን ሦስት ችግር ከመፍታት ይልቅ ጥገናዊ ለውጥ አድርገው መመለስን መርጠዋል" በማለት አስማማው ኃይሉ ይደመድመዋል። በ 'መደምደምያ' (ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ) ደግሞ ደራሲው ማሳሳቢያ ያቀርባል፡- "የኢሕአፓን ታሪክ አጥንቶ ድክመቶችና ጥንካሬውን

ካልተረዱ የዛሬውን ችግር ለመፍታት እጅግ አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም የዛሬዋ ኢትዮጵያ የትናንቱ ታሪክ ቅጥያ ናትና።”

## ነሲቡ ስብሃት (አሉላ) ፍጹም ነው እምነቴ፣ ቀይ ሽብር፣ የከፍተኛ 15 እውነተኛ ታሪክ *ያ ትውልድ ተቋም መስከረም 2007*

ነሲቡ ስብሃት የመጽሐፉን አርእስት *ለዘመናት* ከተሰኘው “የኢሕአፓ የቃል ኪዳን መዝሙር” ነው የወሰደው። ደራሲው የኢትየጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ወጣት ሊግ (ኢሕአወሊ) አባልም ስለነበር የኢሕአፓን የፖለቲካ ፕሮግራም ከመቀበል ባሻገር የፓርቲውን የትግል ስልቶችና ክንዋኔዎችም በግብር ለመተርጎም ቆርጦ ተነስቶ ስለነበር መጽሐፉ “በደርግ ቀይ ሽብር መስዋእት ለሆኑ አባላትና በፓርቲው ላልታቀፉ ሰማእታት በሙሉ፣ የአካልና የስነ ልቦና ጥቃት ሰለባ ለሆኑ ወገኖች…ይሁንልኝ” ይላል። ይህ ዓይነት “መታሰቢያ” በይዘቱና መልእክቱ ከ ኢሕአሡ የዓሲምባ ፍቅር እና ምርኮኛ መጻሕፍት ጋር ተመሳሳይ ነው። ነገር ግን ከነዚህ መጻሕፍት ርእሶች አንጻር ሲታይ የነሲቡ መጽሐፍ አርእስት የኢሕአፓን መዝሙር ጉዲፈቻ ነው ማለት ይቻላል።

መጽሐፉ በከፍተኛ 15 በዘመነ ደርግ በወጣት ኢትዮጵያውያን በደረሰው እስራት፥ ስቃይና ግድያ ላይ ያተኮረ ቢሆንም በጠቅላላ ኢትዮጵያ በቀይ ሽብር ጊዜ በኢትዮጵያውያን ላይ የወረደው ግፍ የሚያንጸባርቅ ነው። በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ደራሲው በርካታ ርእሰ ነገሮችን ያከትታል፣ በከፊልም የሚከተሉት ናቸው፦ ቅድመ ቀይ ሽብር፣ ልጅነት፣ የካቲት 1966 ዓ.ም፣ እድገት በኅብረት፣ የትግል ጉዞ፣ የጥናት ክበብ፣ ደርግና መኢሶን ወዘተ። እነዚህን ርእሰ ነገሮች በይበልጥ ለማጎልመስና የትግሉን ዘመን ለአሁንና ለመጪው ትውልድ ለማስረዳትና (ለማስተማርም ጭምር) መጽሐፉ የሚከተሉትን ዓበይት ነጥቦችን በማንሳት በትረካ መልክ ይገልጻል፦ የኢሕአፓ መሠረታዊ ዓላማዎች፥ አወቃቀርና አካል ድርጅቶች፣ ሚይ ዳይ፣ አደፍርስ፣ ዴሞክራስያ፣ የአብዮታዊ ዘመቻ መምርያ፣ ኡኡታ ኮሚቴ፣ ቀይ ሽብርና የከፍተኛ 15 እስር ቤት ታሪክ፣ ድህረ ቀይ ሽብርና ከፍተኛ 15፣ የማጣራት ጉዞ ወዘተ።

ይህ መጽሐፍ ከሌሎች በኢሕአፓ ላይ ከተጻፉት መጻሕፍት ለየት የሚያደርገው ነገር ቢኖር ደራሲውና ጓዶቹ “የማጣራት ጉዞ” ዓላማ እንደ ተልዕኮ በማንገብ፣ ለመበቀል ሳይሆን ለፍትሕ ባደረጉት ጥረት ድል እንደተቀዳጁ ስለሚያበስር ነው። በከፍተኛ 15 እስር ቤት ውስጥ በነበሩበት ጊዜ የስቃይ ቅጣት ያዘንብባቸው የነበረውን አረመኔው ከፈለኝ አለሙ በደንቨር ኮሎራዶ እንደሚኖር ካረጋገጡ በኋላ ለአመሪካ የጸጥታ ተቋማት ጉዳዩን በማቅረብ ከፈለኝ ፍርድ ቤት ቀርቦ እንዲታሰር አድርገዋል። ከፈለኝ ከኬንያ ወደ አመሪካ እንደ ስደተኛ ሲገባ ስሙ ሀብተአብ በርሄ ተማኑ ብሎ በመቀየርና የኤርትራ የዜግነት ሰነድ በመያዝም ጭምር ነው። ከፈለኝ ያላወቀው ነገር ቢኖር ግን በኢትዮጵያ ያፈሰሰውን ደም ተከትሎት መምጣቱና እርሱና ተባባሪዎቹ “አይቀርለትም መዳኘት፥ አፈር ውስጥ መግባት” የተባለውን የአበው ቢሂል እንደሚደርሳቸው ነው።

ፍጹም ነው እምነቴ ታላቅ መልእክት አላት። በቀይ ሽብር ጊዜ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለስቃይና ለሞት የዳረጉት የደርግ አባላትና ተባባሪዎቻቸው ለፍትሕ መቅረብ አለባቸው። ፍጹም ነው እምነቴ የፍትሕ ያለህ ትላለች።

የገብሩ አስራት መጽሐፍ ለሕዝቡ ከቀረበ በኋላ አንዳንድ ሰዎች ገና ለገና “እሱም ያው ወያኔ ስለሆነ የተለየ ነገር ይዞ አይቀርብም” ያሉ ነበር። “መጽሐፉ መውጣቱን ሰምተናል ግን አናነበውም” ያሉም ነበር። ግን የመጽሐፉ ይዘትና መልእክት ለመደገፍም ይሁን ለመውቀስ እኮ የሚቻለው ሲነበብ ብቻ ነው። መድኀኒት መራራ ሊሆን ይችላል ግን ፈውስ ይሆናል ብሎ ከታመነበት ቢወሰድ ይበጃልና ለወደፊቱ መጽሓፉን ማንበብ ለሚፈልጉ ሁሉ እውቀትን ለመገብየትም ይሁን የተለየ ሐሳብ ለማመንጨት ይረዳ ዘንድ ደራሲው ያቀረበልንን ዓበይት ነጥቦችና በማያያዝም ከዚህ ቀደም ተሰምቶ የማያውቅ ውስጠ ወይራ፣ አንዳንዱ እንቆቁልሽ መሳይ፣ ሌላውም ለማመን የሚያቅት ትረካ በመጽሐፉ ተጠናቅሮ ስለቀረበ ቢነበብ ይሻላል።

ገብሩ አስራት በምዕራፍ አንድ ‘የታሪክ መንደርደርያ’ በሚል ርእስ ስድስት ንዑስ ርእሶችን በማከል ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ያቀርባል። በዚሁ ምዕራፍ የቀረቡ ትረካዊ ትንተናዎች የታሪክ ተመራማሪዎችና ተማሪዎች እንዲሁም መምህራን በቅጡ የሚያውቁት ነው። ምዕራፍ ሁለት “ሕወሐት ኢሕአዴግና የትጥቅ ትግል ዘመን” 22 ንዑስ ርእሶችን ይዞ የቀረበው ግን በሕወሐት (ወያኔ) ዙርያ የነበሩ ታጋዮች የሚያውቁት ጉዳይ ቢሆንም፡ ለሌሎች በወያኔ ያልታቀፉና ወያኔን የማያውቁ ኢትዮጵያውያን እንደ ብርቅ ነገር ብቻ ሳይሆን እንደ ከሳቴ ብርሃን ሆኖ ማገልገል ይችላል። በሌላ አነጋገር ወያኔን በውል ለማያውቁት ኢትዮጵያውያን የሕወሐት አፈጣጠርና ባህርይ በጥልቀት ለማወቅ መጽሐፉ ያግዛቸዋል። በተጨማሪም በዚሁ ምዕራፍና በሌሎቹ ምዕራፉት የተጠቀሱትን ሐቆች በጨለማ ዓለም ለነበሩ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ማለትም የትግራይን ሕዝብ በጅምላ ይኮኑ የነበሩትን አመለካከታቸውን እንዲቀይሩ ይረዳቸዋል።

በምዕራፍ ሦስት “ከመንግሥት ምስረታ እስከ ኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ዋዜማ” እና በምዕራፍ አራት ደግሞ “የኢትዮጵያና ኤርትራ ግንኙነት በጦርነት ጊዜ” በሚሉ ርእሶች ደራሲው እጅግ በጣም የተወሳሰቡ የፖለቲካ ክንውኖች፡ ውሳኔዎችና እንቅፋቶችን በሚመለከት በሰፊው ይተነትናል። ለምሳሌ፣ ሻዕብያ የኢትዮጵያን መሬት መውረሩን ከተረጋገጠ በኋላ “በግንቦት 4 በተካሄዳው የኢሕአዴግ ሥራ አስፋጻሚ ኮሚቴ በሙሉ ድምጽ ኢትዮጵያ ወረራ እንደተፈጸመባት ተስማምቶ ወረራውን ለመቀልበስ የሚያስችለውን እርምጃ ሁሉ ለመውሰድ ውሳኔ አስተላለፈ። በስብሰባው ማጠቃለያ ግን አንድ አወዛጋቢ ጉዳይ ተነሣ። ይኸውም ውሳኔያችን ለፓርላማ ቀርቦ ፓርላማው ውሳኔ ያስተላልፍበት የሚለውን ሐሳብ መለስ ዜናዊ መቃወሙና ጉዳዩ በፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ እና በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጸሕፈት ቤት ቀይቶ መፍትሔ ቢፈለግለት ይሻላል ማለቱ ነበር።”

ምዕራፍ አምስት “የሕወሐት/ኢሕአዴግ ግምገማዎችና ከፍፍሉ” በሚል ርእስ መለስ አዲስ አጀንዳ ይዞ ስለመቅረቡ፣ የብአዴን (ብሔራዊ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ) አመራር በሕወሐት ስብሰባ ካልተሳተፍኩ ማለቱ፣ በመለስና በተቃዋሚዎቹ የቀረቡ ጽሑፎች መኖራቸውንና፣ የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶችን ትጥቅ የማስፈታት እንቅስቃሴ መካሄዱን በዝርዝር ተገልጸዋል።

ምዕራፍ ስድስት “ተሃድሶውና ሰንካዎቹ” የሚል ሆኖ አስር ንኡስ ርእሶችን ለአንባቢ ያቀርብና “በተቀናቃኞች ላይ የተካሄደው የእስር ዘመቻ” እና “ባልታሰሩት ‘አፈንጋጮች’ ላይ የተፈጸሙ በደሎች” ብሎ ይጀምራል። በተካሄዱት ተጨባጭ

ድርጊቶችም ትንታኔውን ለመደገፍ ይጥራል። ሌሎች በዚሁ ምዕራፍ የተጠቀሱ ነጥቦች "ሕወሐት/ኢሕአዴግና የሄጉ የድንበር ኮሚሽን ውሳኔ" እና "ታሪካዊ የ1997 ዓ.ም. ምርጫና መዘዙ" ናቸው።

እንዲህ ዓይነት መጽሐፍ ለመጻፍ ለመጀመርያ ጊዜ ነው በአመራር ደረጃ የነበረው የወያኔ አባል ለሕዝብ ፍጆታ የቀረበው። ከዚህ ቀደም ወያኔ/ኢሕአዴግ አስመልክቶ አነስተኛ መጻሕፍትና መጣጥፎችም ብቅ ጥልቅ ብለው ነበር። ነገር ግን ልዓላዊነትና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ሁሉንምን ነገር ፍርጥርጥ አድርጋ ስላወጣችው በአንባብያን ዘንድ ከፍተኛ እንድምታ እንደሚኖራት ጥርጥር የለውም። በተጨማሪም የዚሁ ዓይነት መጽሐፍ ደርሶ ለአንባብያን ማቅረብ መርህና ቆራጥነትን ይጠይቃል።

የመጽሐፉን ይዘት ወይም በመጽሐፉ የቀረቡ አንዳንድ መረጃዎች ስሕተት ናቸው የሚሉ አንባብያን ካሉ ማስታወሻ ወይም ሒሳዊ አስተያየት ይላኩልንና በዚሁ ድረገጽ እንለጥፈዋለን። የዴሞክራሲ አንዱ መገለጫም ይኸው ነው። ይኸንን ለማበረታታት የፈለግነውም፣ ለእንካ ስላንትያ ሳይሆን፣ በኢትዮጵያችን መልካም የፖለቲካ ባህል እንዲሰፍን ለመጠቆምም ጭምር ነው። ለምሳሌ በዚሁ መጽሐፍ ደራሲው ከኢሕአፓና ወያኔ ጦርነት በኋላ የኢሕአፓ ሠራዊት ጀብሃ በሚቆጣጠረው የኤርትራ መሬት ውስጥ ለሁለት ዓመት ተጠልሎ እንደቆየ ያትታል። ይህ ግን ስሕተት ነው። ሠራዊቱ ለሥስት ወራት ብቻ ነው ኤርትራ ውስጥ የቆየው። ይኸም የሆነበት ዋና ምክንያት ተከዜ ከመጠን በላይ ሞልቶ ስለነበር ሠራዊቱን በቀላሉ ማሻገር ስላልተቻለ ነበር። ሌላም ኢሕአፓን አስመልክቶ በመጽሐፉ አንዳንድ ግድፈቶችና ክፍተቶች ተንጸባርቀዋል። ነገር ግን ስሐተቶቹ በቂ መረጃ ካለማግኘት የተፈጸሙ ናቸው የሚመስሉት፣ ስለሆነም የመጽሐፉ ግዙፍ ትንተናና መልእክት አይቀይሩትም።

የአፍሪቃ ልማትና ተምህርት ተቋም (አልትተ) የባለቤትነት መብት በሕግ የተጠበቀ ነው። All Rights Reserved. Copyright © Institute of Development and Education for Africa (IDEA), 2014